# የተመረጡ ፍርዶች

የሰ/መ/ቁ.102662

የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ ዓሊ

መሐመድ ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ለሼ- ጠበቃ ኤርሚያስ ደስታ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ በቀለ በላቸው- ወኪል ትርፍነሽ በቀለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ጋብቻ ፈርሷል ሊባል የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደብረብርሃን ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ክሱን ያቀረቡት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ከአሁኑ ተጠሪ ጋር በአገር ባህል የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓት ጋብቻ ፈጽመው ለአርባ አመታት ያህል አብረው መኖራቸውን፣ ይሁን እንጂ ከመስከረም 2006 ዓ/ም ጀምሮ ሊስማሙ ባለመቻላቸው በመካከላቸው ሰላም እንደሌለ ገልፅው ጋብቻው ፈርሶ የጋራ ንብረት እንዲካፈሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ከአመልካች ጋር ባልና ሚስት የነበሩ መሆኑን ሳይክዱ አመልካች ከአስራ ዘጠኝ አመታት በፊት ቤቱን ጥለው መሄዳቸውንና ተለያይተው የሚኖሩ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያስቀደሙ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ ከአመልካች ጋር ያፈሩት የጋራ ንብረት የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ክ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ ከአስር አመታት በፊት ፈርሷል የሚል ድምዳሜ ደርሶ የአመልካች ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሑፍ አከራክሯል፡፡እንዲሁም የወረዳው ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ እንዲመጣ አድርጓል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በተጠሪና በአመልካች መካከል ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ተገቢነት አለውን? የሚለው ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ በአመልካችናበተጠሪ መካከልየነበረውጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል በማለት በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር አልተቀበለውም፡፡

ፍርድ ቤቱ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የጋብቻ ግንኙነታቸው ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ ተቋርጦ ግራ ቀኙ ለየብቻ መኖር መጀመራቸው ተረጋግጧል በሚል አቢይ ምክንያት ነው፡፡ ይህ የወረዳው ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ የሆነ ስልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት አጥብቀው የሚከራከሩት ግራ ቀኙ ሌላ ትዳር መስርተው የራሳቸውን ሕይወት የማይኖሩ መሆኑን፣ አልፎ አልፎ በጤና ምክንያት አመልካች ለፀበል ወደ ሌላ ቦታ ከመሄዳቸው ውጪ አመልካችና ተጠሪ ያልተለያዩና እስከ መስከረም 2006 ዓ/ም ድረስ አንድ ላይ የሚኖሩ መሆኑን ዘርዝረው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው አስገዳጅ ውሳኔ ተጠቅሶ መወሰኑ ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14290፣ 20983፣ 31891፣ 67924 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ከሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ የወረዳው ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገውና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 31891 ሌሎች ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት በሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች በባልና ሚስት መካከል ያለ ጋብቻ በፍ/ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ ፈርሷል ባይባልም የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረጅም ጊዜ መኖር፣ በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መሥርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ ተቋርጧል ሊያስብል ይችላል በማለት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህም ውሳኔ ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው የጋብቻ መፍረስ በተጋቢዎች የረዥም ጊዜ መለያየት ሊከናወን የሚችል መሆኑና ፍርድ ቤቱም በዚህ አግባብ የፈረሰውን ጋብቻ እንደገና እንዲፈርስ ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ነው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 67924 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ አግባብ የመተጋገዝና የመተባበር ግዴታቸውን ሲወጡና የነበሩና ያልተለያዩ መሆኑ ከተረጋገጠ ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ለማለት የማይቻል መሆኑን በመዝገቡ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች በመነሳት የተወሰነ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካችና ተጠሪ በሕጉ አግባብ ጋብቻ መሰርተው ልጆችን ከወለዱ በኋላ በ1987 ዓ/ም ጀምሮ በአካል ተለያይተው ለአስራ ዘጠኝ አመታት ያህል ሳይገናኙ የኖሩ መሆኑን ከግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል የተረጋገጠ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ደምድመዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀረበው የወረዳው ፍርድ ቤት

ዋና መዝገብም የግራ ቀኙ ምስክሮች የመሰከሩት የፍሬ ነገር ነጥብ በይዘቱ የበታች ፍርድ ቤቶች ከደመደሙት ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ተገንዝቦአል፡፡

በመሆኑም አመልካች ከተጠሪ ጋር እስከ መስከረም 2006 ዓ/ም ድረስ አልተለያየንም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታ በስር ፍርደ ቤት ዋና መዝገብ ውስጥ በምስክሮች ከተነገረው የምስክርነት ቃል ይዘትና ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ከደረሱበት ድምዳሜ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች አግባብ የተሰጠውን ስልጣንም ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ ጋብቻ በተጋቢዎች መካከል የመተጋገዝ፣የመከባበርና መደጋገፍ እንዲሁም አብሮ የመኖር ግዴታን የሚጥል መሆኑን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 60 እና 61 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

ከዚሁ አኳያ በተጠሪና በአመልካች መካከልየነበረው ጋብቻ ይህ ሰበር ችሎት አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ተቋርጧል? ወይንስ አልተቋረጠም? የሚለውን ለመወሰን ከፍ ብሎ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በጋብቻ ውስጥ በግራ ቀኙ የሚጠበቁ ግዴታዎች ባግባቡ ሲተገበሩ ያልነበሩና እነዚህን ግዴታዎችን ለመወጣት ደግሞ በአመልካች በኩል ያጋጠመው ሁኔታ በሕጉ የተጣሉባቸውን ግዴታቸውን ለመወጣት የማያስችል የነበረ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ከተጠሪ ጋር አልተለያየንም፣ በጤና ችግር ምክንያት አልፎ አልፎ ለፀበል ሌላ ቦታ እሄድ ነበር በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በክርክሩ ሂደት በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን መሰረት አድርጎ ያልቀረበ ሁኖ አግንተነዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በተያዘው መዝገብና ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸው መዛግብት የያዟቸው መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ከዚህ መዝገብ ከተረጋገጡት እውነታዎች ሙሉ በሙሉ የተመሳሳይነት ያላቸው ሁኖ እያለ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ሌላ ትዳር መስርተው ሕይወታቸውን በመምራት ላይ አይገኙም በማለት በሰ/መ/ቁጥር 31891 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመተውና ግንኙነቱ ያልተቋረጠ ተጋቢዎችን መሰረት ተደርጎ በመ/ቁጥር 67924 የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ አመልካች መከራከራቸው ከአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) አተገባበር ጋር የሚጋጭ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ በሁኔታ የፈረሰ በመሆኑ እና ለጉዳዩ አግባብነት በላቸው ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት በተሰጠው ትርጉም መሰረት የጋራ ንብረት ጥያቄም በአስር አመት ያልቀረበ በመሆኑ የተጠሪ ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ብይን መስጠቱ የሚነቀፍበትን የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሁኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0108191/06 በ22/08/2006 ተሠጥቶ በሰሜን ሸዋ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0114418 በ30/08/2006 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 030-5041 ግንቦት 19 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል በአገር ባህል የጋብቻ አፈፃጸም ስርዓት ተመስርቶ የነበረው ጋብቻ ለረዥም ጊዜ ተለያይቶ በመኖር ምክንያት ፈርሷል በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ትዕዛዝ**

ከደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርደ ቤት የመጣ መዝገብ ቁጥር 0108191/06 በመጣበት አኳሀን ይመለስ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

የሰ.መ.ቁ. 08862

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፤ ፀጋዬ ወርቅአየሁ

ጌትነት መንግስቴ

ፍቅሬ ጥላሁን

አንዳርጌ ላቀ

ዩሐንስ ቢሻው

አመልካች ----------------- የአ.ብ.ክ.መ ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ቀረቡ

ተጠሪ --------------------- አውግቸው መኮነን ጠበቃ ተሾመ መኮንን ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ተጠሪ መልስ የሚያቀርብ ቢሆን ለመጠባበቅ ነው፡፡ የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ/ም የተፃፈ ሰባት ገጽ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ አመልካች የተጠሪው ጉዳይ ታይቶ ያስቀርባል የተባለበት ነጥብ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ስለሆነ ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲከታተልልን ሆኖ ለዚህም የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ተጠሪን ካለበት አድራሻ አፈላልጐ እንዲያቀርበው እንዲደረግልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ በበኩላቸው ጉዳዩ እየታየ ያለው በይግባኝ ደረጃ በመሆኑ በሥ/ሥርዓት ህጉም ሆነ በሥነ ምግባር አዋጁ ላይ በይግባኝ ደረጃ ባለ ክርክር ተከራካሪዎች ዋስትና እንዲነፈጋቸው የሚያደርግ ባለመሆኑ የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤ ይህ የሚታለፍ ቢሆን ይህ ፍ/ቤት የማያየው ተጠሪ ሊከራከር ይገባ ነበር አልነበረም በሚለው ነጥብ ላይ በመሆኑ ተከላከል ከመባሉ በፊት ዋስትና እንዲነፈገው የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ከሁሉም በላይ ደግሞ ተከላከል ቢባል እንኳ አንቀጽ ሊቀየርና ዋስትና ሊያስፈቀድ በሚችል አንቀጽ ሊቀይረው ስለሚችል ተቃውሞው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ብለናል፡፡ በግራ ቀኙ በኩል የቀረቡትን መከራከሪያዎች አግባብነት ካላቸው ህጐች ጋር በማገናዘብ መርምረን ተከታዩን ብይን ሠጥተናል፡፡

ብ ይ ን

አመልካች ተጠሪው በሥር ፍርድ ቤት የተከሰሱበትና በዚህ ችሎት ይስቀርባል ተብሎ በመታየት ላይ ያለው ጉዳይ ከአሥር ዓመት በላይ በሆነ እስራት የሚያስቀጣ ስለሆነና ይህም የሚያስከለክል በመሆኑ ተጠሪን የክልሉ ፖሊስ ከአለበት በመያዝ ለማረሚያ ቤት እንዲያስረክበው ጠይቀዋል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ በበኩላቸው በዚህ ደረጃ ላለ ክርክር የሥነ ሥርዓት ህጉም ሆነ የሥነ-ምግባር አዋጅ ዋስትና እንዲነፈጋቸው የሚያደርግ አይደለም፤ ይህ ቢታለፍ እንኳን ጉዳዩ ታይቶ ተጠሪ ይከላከል ሲባል ድንጋጌው ካልተቀየረ የሚፈፀም ስለሆነ በአመልካቹ የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ባይ ናቸው፡፡

ለቀረበልን ጥያቄ እና በጥያቄው ላይ ለቀረበው መቃወሚያ ብይን ከመስጠታችን በፊት ጉዳዩን ምንነት እና አመጣጡን ከመዝገቡ ግልባጭ ገባ ብለን አይተናል፡፡ እንዳየነውም ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አምስት የተለያዩ ክሶች በአንድ መዝገብ ተመስርቶባቸው ከነዚህ ክሶች ውስጥ ለአቤቱታው ምክንያት በሆኑት ሶስት ክሶች መከላከል ሳይስፈልጋቸው በነፃ እንዲሠናበቱ ተወስኗል፡፡ ይህ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ይህ ሠበር ሰሚችሎት ደግሞ በአመልካች የሠበር ቅሬታ አቅራቢነት ታይተው በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢፌድሪ የወንጀል ህግ 407/2/ እና 408/2/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፈዋል በሚል በተጠሪ ክስ ቀርቦ መከላከል ሳይስፈልጋቸው በነፃ እንዲሠናበቱ በሥር ፍ/ቤቶች የተሠጠውን ውሣኔ ተገቢነት ለማጣራት በሚል በሁለቱ ክሶች ተጠሪ መልስ እንዲሠጡበት ሆኖ ጉዳዩ ለምርመራ ባደረበት ሁኔታ ነው ይህ የዋስትና ክርክር የቀረበልን፡፡

እኛም ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት የተከሠሱበት እና አሁን በሠበር ያስቀርባል የተባሉት የወንጀል ድንጋጌዎች የተከሠሠን ሰው የዋስትና መብት የሚያስከለክሉ ናቸውን? ናቸው የሚባል ከሆነስ ህጉ በመጀመሪያ ደረጃ በሚታይ የክስ ክርክር እና በይግባኝ ወይም በሠበር ደረጃ በሚኖር ክርክር ልዩነት ይፈጥራል ወይ? የሚሉትን ነጥቦች በመጨበጥ ምላሽ ለመስጠት ለጉዳዩ ዕልባት መስጠት ያስችላሉ ብለን አምነናል፡፡

በዚህ መሠረት እንዳየነው አሁን በሠበር ደረጃ እየታዩ ያሉትና ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሰው በነፃ እንዲሠናበቱ የተወሰ ነው በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢፌድሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 407/2/ እና 408/2/ የተጠቀሱባቸው ሁለት ክሶች ናቸው፡፡

በኢፌድሪ መንግስት የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ዓ/ም አንቀጽ 4/1/ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎች የተከሠሡበት ወንጀል ከአስር አመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መልቀቅ አይቻልም ሲል ደንግጓል፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ በሠበር ችሎት ያስቀርባል ተብለው እየታዩ ካሉት ሁለት ክሶች ውስጥ አንደኛው ብቻ ከአስር ዓመት በላይ ያስቀጣል፡፡ ወንጀሎቹም በወንጀል ህጉ ምዕራፍ 2 ስር የሙስና ወንጀል ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ የሚካተቱ በመሆኑ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ተከሠው በፍ/ቤቶቹ በነፃ የተሠናበቱበት ውሣኔ አግባብነት በዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ በመታየት ላይ ያለው ጉዳይ በዋስ የመለቀቅ መብትን የሚነፍጉ ናቸው ብለናል፡፡

ሆኖም ግን በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ጉዳይን በሚመለከት በተጠሪ ጠበቃ የሥነ ሥርዓት ህጉም ሆነ በሥነ ምግባር አዋጅ አንድ በዋስትና የሚያስከለክሉ ክሶች በሠበር ደረጃ ሲታይ ተፈፃሚ እንዲሆን አልደነገጉም የሚል መከራከሪያ ቀርቧል፡፡ ይህ መከራከሪያ በጠበቃው በግልጽ ባይነሣም ህጉ የተከሠሡ ሰዎች ዋስትና ተከልክለው በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን የሚከታተሉበት አግባብ የደነገገው በመጀመሪያ ደረጃ ክሱ በፍ/ቤት በሚታይበት ጊዜ ነው፤ በይግባኝ ወይም በሰበር ደረጃ በሚሆንበት ጊዜ ህጉ በዝምታ ያለፈው ከመሆኑ እና ተያያዥነት ባላቸው ሌሎች መነሻዎች የመነጨ ነው የሚል ግምት አለን፡፡

በእርግጥ በ1954 ዓ/ም የወጣው የኢትዩጳያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ሥርዓት ህጉ ዋስትና በሚያስከለክሉ ወንጀሎች የተከሠሡ ሰዎች በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን የሚከታተሉበት ድንጋጌ ያለው በህጉ ሁለተኛ መፀሀፍ የመክሰስና የምርመራ ሥነ ሥርዓትን በሚለከተው ምዕራፍ ሶስት ውስጥ ነው፡፡ ይህ አይነት ድንጋጌ ጉዳዩ በይግባኝ ወይም ከዚህ በላይ በሚኖረው ክርክር በድጋሚ አልተካተተም፡፡ በተመሣሣይ በተሻሻለው የሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ስለዋስትና ክልከላ የሚደነግጉት ድንጋጌዎች የተዋቀሩት ስለዋስትና የፍርድ ቤት ስልጣን የሚል ርዕስ በተሠጠው የአዋጅ ክፍል ሁለት የተከታተ ሲሆን ድንጋጌው በይግባኝ ደረጃ ተፈፃሚ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ሣይደነግግ በዝምታ አልፎታል፡፡

በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ሠወች በዋስ የመፈታት መብት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19/6/ የተፈቀደ ሲሆን በሚከሠሡበትም ጊዜ እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት /አንቀጽ 20/3/ የተከበረ መብት ነው፡፡ ይሁን እንጅ ህገ መንግስቱ አንቀጽ 19/6/ በህግ በልዩ ሁኔታዎች በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄን ላለመቀበል እንደሚችል ደንግጓል፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይም ቢያንስ በመጀመሪያ ደረጃ ለሚኖር ክርክር በዋስ የመለቀቅ መብት በህግ የተገደበ መሆኑን አይተናል፡፡ አጠያያቂው ጉዳይ ይህ ክልከላ ተፈፃሚነቱ በይግባኝ ወይም በሠበር ደረጃ ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡

አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በሚጠረጠርበት ጊዜ ከምርመራ ጀምሮ በፍርድ ወይም በፍትህ ስርዓቱ የመጨረሻ ውሣኔ ሰጭ አካል አይቶ የግለሠቡን ነፃነት ወይም ጥፋተኛነት የሚኖርን የሥራ ሒደት ለማሣየት ነው የወንጀለኛ መቅጫ ህጉም ሆነ የሙስና ልዩ የሥነ- ሥርዓት ህጉም ወጡት፡፡ የአንድ የወንጀል ተጠርጣሪ ጉዳይ የምርመራም ሆነ የፍርድ ሂደት የሚመራው የሥነ- ሥርዓት ህግ/ህጎች/ በሚያዋቅሩት አንድ የስራ ሂደት ነው ካልን እንደ ጥቅም፤ ምርመራ፤ ክስ፤ የክስ ሂደት፤ ፍርድ፤ ቅጣት፤ ይግባኝ፤ የይግባኝ ክርክር ውሣኔ፤ የሠበር አቤቱታ፤ የሠበር ክርክር የሠበር ውሣኔ ወዘተ-- የሚሉት በሂደቱ ያሉ ደረጃዎች ሲሆኑ አንዱ ለሚቀጥለው መሠረት ሆኖ በአብዛኛው በቅደም ተከተል የተቀመጡናቸው፡፡ ይህ ባህሪያቸው ለምሣሌ በፍርድ ሂደት ባሉ ደረጃዎች ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ ባለክስ ስለከሣሽም ሆነ ስለተከሣሽ የተደነገጉ መብትና ግዴታዎች ቀጥሎ ለሚኖሩት እንደ ይግባኝ ባሉ ደረጃዎች በልዩ ሁኔታ እስካልተደነገገ ድረስ እንደጠቅላላ መርህ ተወስደው ተፈፃሚነታቸው እስከ መጨረሻው የሚቀጥል ነው፡፡

ስለሆነም ህግ አውጪው ለአንድ ጉዳይ ሲል ሲደርስበት ያሰበው ዓላማ ካለ አንድ ተከሣሽን በአንድ የፍርድ ሂደት የነገሩ ጭብጥም ሆነ የተከራካሪዎች ማንነት ሣይለወጥ ለወሰደው የፈለገው የጥንቃቄ እርምጃም ሆነ ሊደርስበት ያለመው ግብ የክስ ሂደቱ ከመጀመሪያ ክሱ ወደ ይግባኝ ብሎም ወደ ሠበር ደረጃ ሲሸጋገር አንድ መሆኑ እስከቀጠለ ድረስ ህጉ በመጀመሪያ ክስ ሂደት ዋስትና ስለመከልከል ደንግጐ በድንጋጌው ሊወሰደው ያሰበው የጥንቃቄ እርምጃና ግብ እስካልተለወጠ ድረስ ተፈፃሚነቱ እስከ መጨረሻው ደረጃ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡

የተከሰሱ ሰዎች በተወሰኑ የወንጀል አይነቶች በዋስ የመለቀቅ መብታቸው ቀሪ ሆኖ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ ህግ አውጭው ለወሰደው የፈለገው የጥንቃቄ እርምጃም ሆነ

ሊደርስበት ያሰበው ግብ አንድ በወንጀል ተከስሶ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ በነፃ ከተሠናበተ በኃላም ከወንጀሉ ነፃ የመሆኑ አጠያያቂ ስለመሆን ከበላይ ባሉ ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ፍ/ቤቶች/ችሎት/ ሲታመንበት በሚኖር ክርክር ጊዜም ተመሣሣይና የማይለዋወጡ ናቸው፡፡

በመሆኑም በተጠሪ ጠበቃ በኩል ህጉ በይግባኝ ደረጃ በዝምታ የዋስትና ጉዳይን ማለፉን አጽንኦት ሰጥተው ደንበኛቸው በውጭ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ጠበቃው በአማራጭ ያቀረቧቸው መከራከሪያወች ከላይ የታየው ዋናው መቃወሚያቸው አወንታዊ ምላሽ ማግኘቱን ታሣቢ በማድረግ በመሆኑና የችሎቱ ምላሽ አሉታዊ በመሆኑ ማየቱ አላስፈለገንም፡፡

ሌላው በተለይ ሙስናን በሚመለከት ፍ/ቤት በመፍቀድ ወይም በመከልከል በሚሠጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማለት እንደሚችል በመለቀቁ ላይ ይግባኝ ከተባለ ብቻ/አንቀጽ 5/2/ ልዩ የሥነ ስርዓት ህጉ የመለቀቁ ውሣኔ ይታገዳል ከተባለ ይህ ግለሰብ ክስ ቀርቦበት ከክሱ በነፃ ሲሰናበት እና የመሰናበቱ አግባብነት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጥያቄ ውስጥ ሲገባ ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣት ዕድሉ እንደመጀመሪያው ሁሉ ሀምሣ፤ ሀምሣ በመቶ ስለሚሆን በዚህ ሁኔታ ከእስር እንደተለቀቀ የነገሩ መታየት ይቀጥላል የሚለው ሀሣብ ምክንያታዊ ያልሆነ እና ከህጉ ዓላማ ውጪ ነው የሚል እምነት አለን፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ ተላልፈዋል ተብለው ለዚህ ክርክር ምክንያት የወንጀል ድርጊት የዋስትና መብትን የሚያስነፍግ ሆኖ ሣለ ጉዳያቸው በሠበር ደረጃ በመታየቱ ብቻ የዋስትና መብት መከልከል በደንበኛቸው ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆን ያቀረቡት መቃወሚያ የህግ መሠረት የሌለው ስለሆነ ተጠሪው ጉዳያቸው ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን ሊከታተሉ ይገባል ብለናል፡፡ ብይኑ በአብላጫ ድምጽ የተሠጠ ነው፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1- ተጠሪን የክልሉ ፖሊስ ከአሉበት አፈላልጎ በመያዝ ለማረሚያ ቤት እንዲያስረክባቸው ታዝዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

2- ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት አስቀድሞ መርምሮ ለመወሰን የተየዘው ቀነ ቀጠሮ አልተለወጠም፡፡

ያስቻሉት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የሐሳብ ልዩነት

ስሜ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር አንድ የተገለፀው ዳኛ በአብላጫው ድምጽ በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው እገልፃለሁ፡፡

ተጠሪ የተከሰሰበት ወንጀል ከመሠረቱ ዋስትና የሚያስከለክል ነው፡፡ በዚህ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ በነበረው ክርክር የዋስትና መብቱ ተነፍጎ ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ ሲከታተል ቆይቷል፡፡ በመጨረሻም የዓቃቤ ህግ ማስረጃ ተመዝኖ ተጠሪ በነፃ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡

በውሳኔው ዓቃቤ ህግ ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ባቀረበ እና አቤቱታው በበላዩ ፍርድ ቤት ታይቶ ያስቀርባል በተባለ ጊዜ ክርክሩ ዕልባት አገኘ ድረስ የተጠሪ ቆይታ ምን ይሆናል በሚለው ላይ ፍርድ ቤቶች የተለያዩ አቋሞች ሲያንጸባረቁ ይታያል፡፡ በኔ እምነት ይህን የመሰለ ጥያቄ ለመመለስ መነሻው የወ.መ.ሥ..ህ.ቁ. 193 መሆን እንዳለበት ይሰማኛል፡፡ ይህ ድንጋጌ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመልስ ሰጭነት የሚከራከሩ መልስ ሰጭዎች በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ራሳቸው ወይም ጠበቃቸው ያልቀረቡ እንደሆነ ክርክሩ በሌሉበት ስለሚቀጥልበት ሁኔታ ይናገራል፡፡ በይግባኝ ክርክሩ እንዲቀጥል ለማድረግ መልስ ሰጭ ወይም ጠበቃው መቅረባቸው ብቻ በቂ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በይግባኝ ክርክር ጊዜ የመልስ ሰጭዎች በአካል መገኘት አስፈላጊ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው (appearance is not mandatory)፡፡ የክርክሩ ምክንያት ከመሠረቱ ዋስትና የሚያስከለክል ቢሆንም ባይሆንም መልስ ሰጭ የሆነው ሰው እንዲቀርብ ህጉ ግዴታ አይጥልበትም፡፡ ባይቀርብም እንኳ ጉዳዩ በሌለበት ሊታይ የሚችል በመሆኑ ተጠሪ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ ስለሚደረግበት ሁኔታ መነጋገር አይቻልም፡፡ በዚህ ምክንያት የተጠሪ ዋስትና ተነፍጎ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ ይደረግልን የሚለው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ዋስትና ህገ-መንግስታዊ መብት ነው፡፡ አይገደብም ማለት ግን አይደለም፡፡ የህብረተሰቡ ጥቅም ሊነኩ ይችላሉ በሚባሉ ዋና ተብለው በተለዩት የወንጀል ዓይነቶች እና በሌሎች በልዩ ሁኔታ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ከፍርድ በፊት ዋስትና ሊከለከል ይችላል፡፡ ከፍ ያለ ጉዳት በህብረተሰቡ ላይ እንዳይደርስ ለመከላከል ነው፡፡ ይህን በመሰለ ሁኔታ የግለሰቦች ነፃነት እንዲገደብ ህብረተሰቡ ይሻል፡፡ በጠቅላላው ህብረተሰብና በግለሰቦች ጥቅም መካከል ያለውን የጥቅም ግጭት ለማስታረቅ የተቀመጠ ሚዛን ነው፡፡ ይህ ግን በመጀመሪያ ደረጃ ለሚደረጉ ክርክሮች የሚያገለግል ነው፡፡ በይግባኝ ደረጃ ሲሆን ነገሩ ይለወጣል፡፡ ይግባኝ የክለሣ ሥርዓት ነው፡፡ በመሆኑም መጠነኛ ልዩነቶች አሉት፡፡ ይህንን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በይግባኝ ክርክር ጊዜ መልስ ሰጭ መቅረብ ሳያስፈልገው ጠበቃው ከቀረበ ይኸው በቂ ሆኖ ክርክሩን መምራት ይቻላል፡፡ ዓላማው በመጀመሪያ ደረጃ ክርክር የግለሰቦችን ነፃነት ለመገደብ ምክንያት የሆነው ስጋት በይግባኝ ክርክር ጊዜ የማይኖር፣ ቢኖር እንኳ በእጅጉ የሚቀንስ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የመልስ ሰጭ በአካል መገኘት እምብዛም አስፈላጊ አይሆንም፡፡ ይህን የምልበት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃው ክርክር ከሳሹ የሰበሰበው ማስረጃ ከመቅረቡና ከመመዘኑ በፊት ተከሰሾች በዋስትና ቢለቀቁ በህብረተሰቡ ጥቅም ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ሊደርስ ይችላል የሚል ግምት በመኖሩ ዋስትና መከልከሉ ተገቢ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን መዝኖ በነፃ እንዲሰናበት ከወሰነለት፣ ነፃነቱ በፍርድ ከተረጋገጠለት በኋላ ግን መልስ ሰጭ እንደመጀመሪያው ክርክር ሁሉ ለህብረተሰቡ የነበረው አስጊነት በዚያው ደረጃ ይቀጥላል ተብሎ የሚታሰብ ስለማይመስለኝ ነው፡፡ የተሰበሰበቡት የከሳሽ ማስረጃዎች ከመመዘናቸው በፊትና ነጻ እና ገለልተኛ በሆነው ፍርድ ቤት ተመዝነው መልስ ሰጭዎች በነፃ ከተሰናበቱ በኋላ የመልስ ሰጭዎች አስጊነት በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ይገኛል የሚል ዕምነት የለኝም፡፡ ማስረጃው ተመዝኗል፡፡ ጥፋተኛ ለማድረግ የሚያበቃ ሆኖ ግን አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ከፍርድ በፊት የነበረው የህብረተሰቡ የመጀመሪያ ስጋት በፍርድ ሂደት የመልስ ሰጭ ነፃነት ከተረጋገጠ በኋላ በነበረበት ሁኔታ አይቀጥልም፡፡ በይግባኝ ደረጃ ሥጋት አይኖርም ማለት ነው፡፡ ሥጋቱ ቢኖር እንኳ

ከፍርድ በፊት በነበረው ሁኔታ ስጋቱ ጥበቃ በሚያስፈልገው ደረጃ የግለሰቦችን ነፃነት እንዲገደብ ለማድረግ የሚያበቃ አይሆንም፡፡ እንዲህ ሲሆን የህብረተሰቡ ፍላጎት የግለሰቦች ነፃነት እንዲገደብ ከመፈለግ ይልቅ የፍርድ ቤቱ ውሳኔዎች እንዲከበሩ ጽኑ ፍላጎት አለው፡፡ ህብረተሰቡ ደህነቱን ከፍ ያለ ስጋት ላይ እንዳይወድቅ የሚፈልገውን ያህል በዕኩል ደረጃ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲከበር፤ አስተማማኝነት እንዲኖረውም ይፈልጋል፡፡ ነጻ እና ገለልተኛ ሆኖ የሚሠራ፣ ዕምነት የሚጣልበት ፍርድ ቤት ያቋቋመውም ለዚሁ ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪን ነፃነት የሚያረጋግጠውን የፀና ውሳኔ በይግባኝ እስኪቀየር ድረስ ማክበር ይገባል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦ በመታየት ላይ በመሆኑ ብቻ ውሳኔው እንዳልተሰጠ ተቆጥሮ የመልስ ሰጭ ዋስትና ጥያቄ ውስጥ የሚወድቅበት ሁኔታ የለም፡፡ በይግባኝ በቀረበው ክርክር ተጠሪው አሊያም እርሱ መቅርብ ሳያስፈልገው በጠበቃው አማካኝነት ሊከታተል እንደሚችል መደንገግ ያስፈለገው ለዚሁ ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ዋስትና መነፈግ አለበት፤ ጉዳዩም ዕልባት አገኝ ድረስ በማረሚያ ቤት መቆየት አለበት ሊባል አይገባም፡፡ በዚህ የተነሳ የመልስ ሰጭ ዋስትና ተነፍጎ ማረሚያ ቤት እንዲቆይ ይደረግልኝ የሚለው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይሆንም፤ የህጉ ፍላጎት አይደለም የምለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በፀረ-ሙስና ህግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 5 ላይ በይግባኝ በመታየት ላይ ባሉ ጉዳዮች የተከሳሾች የዋስትና መብት ተነፍጎ በማረሚያ ቤት ሊቆዩ ስለሚችልበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በምን ዓይነት ጉዳዮች ላይ የሚለውን ማየት ያስፈልጋል፡፡ በኔ ዕምነት ድንጋጌው ራሱን የቻለ የዋስትና መዝገብ ተከፍቶ ወይም በመጀመሪያ ደረጃ የፍሬ ነገር ክርክር ቀርቦ በዚህ የክርክር ሂደት በቀረበ የዋስትና አቤቱታ ላይ ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ ስለሚጠይቅበት ሁኔታ የሚገልጽ ነው፡፡ የዋስትና ጥያቄ ዋና መከራከሪያ ሆኖ ይቀርባል ማለት ነው፡፡ እንዲህ ባሉ ሁኔታዎች በዋስትናው ላይ መከራከሩ ትርጉም እንዳያጣ፣ ህጉ ጥበቃ ማድረግ የፈለገበት ዓላማም እንዳይሳት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይፈፀም እንዲቆይ መባሉ ነው፡፡ ያሳምናል፡፡ ህጉ የሚናገረነውም ስለዚህ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ግን የተጠቀሰው ህግ የመጀመሪያ ደረጃ ክርክር ታይቶ በፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በጥፋተኛነት ውሳኔው ላይ የሚቀርብ የይግባኝ ክርክርን የሚመለከት አይደለም፡፡ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡ ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶች እንዲህ ያለው ጉዳይ የሚመራው በመደበኛው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ነው፡፡ በዚህ ህግ መሠረት ደግሞ ተጠሪ በጠበቃው አማካኝነት ጉዳዩን በመከታተል ላይ ከሆነ፣ ባይከታተል እንኳ በሌለበት ጉዳዩን ማየት እየተቻለ ዋስትናው ተነፍጎ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ ይደረግልን የሚለው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይመስለኝም፡፡

ስለሆነም የአብላጫው ድምጽ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተጠሪን ዋስትና ለማስነፈግ አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ሊቀበለው አይገባም ነበር በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በሃሳብ የተለዩት ዳኛ ፌርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ. 06939

መጋቢት 13 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዓለሙ ተደበበ

ፀጋዬ ወርቅአየሁ

ጌትነት መንግስቴ

ተፈሪ ገብሩ

ጌታዬ እንዳለው

አመልካች..........መሠረት ታዬ ቀረቡ

ተጠሪ..........እማሆይ ፈለጉሽ መለሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

ከመዝገብ ምርመራው እንደተረዳነው ክርክሩ የተጀመረው በባህር-ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የሚከራከሩት በውርስ ሃብት ነው፡፡ ተጠሪዋ የሟች ልጇ አበበ አሰሜን ሃብት ባለቤቱ የሆነችው አመልካች ይዛለችና ድርሻዬን ልትሰጠኝ ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም በክሱ ላይ የተጠቀሱትን ንብረቶች በተመለከተ ይበጀኛል የሚሉትን መከራከሪያ በዝርዝር በማንሳት የበኩላቸውን ሙግት አቅርበዋል፡፡

በዚህ የክርክር ሂደት ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነችው ኮድ 3 የታርጋ ቁጥር 04539 አ.ማ. የሆነችው ባለ አሥራ ሁለት መቀመጫ ሚኒባስ መኪና በተጠሪ አመልካችነት ሳትሸጥ፣ ሳትለወጥ፣ ወይም በማናቸውም መንገድ ለሦሥተኛ ወገን ሳትተላለፍ ተከብራ እንድትቆይ እንዲደረግ ታዟል፡፡

ይሁንና ተጠሪ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ አመልካች በመኪናው መገልገላቸውን ያልገታ በመሆኑ በመኪናው በብቸኝነት መገልገላቸው እንዲቆም ለማድረግ መኪናዋ አገልግሎት መስጠት እንድታቆም ሊደረግልኝ ይገባል በማለታቸው ፍርድ ቤቱ በአቤቱታቸው መሠረት እንዲፈፀምላቸው ትዕዛዙን ለባህር-ዳር ትራፊክ ፖሊስ ጽ/ቤት ታህሣሥ 12 ቀን 2002 ዓ.ም አስተላልፎላቸዋል፡፡

ከሦሥት ቀን በኋላም ታህሣሥ 15 ቀን 2002 ዓ.ም አመልካች ቀርበው አገልግሎት መስጠት እንድታቆም ትዕዛዝ የተላለፈባት መኪና በባንክ ዕዳ የተገዛች በመሆኗ ዕዳውን በወቅቱ ለመክፈል እንዳንችል ሆነናል በማለታቸው ፍርድ ቤቱ የተጠሪን አስተያየት ሳይጠብቅ መኪናዋ አገልግሎት እንዳትሰጥ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ አንስቷል፡፡

ይህ ትዕዛዝ በተሰጠ በስድስተኛው ቀን ተጠሪ ቀርበው አመልካቾች መኪናዋን ያለአግባብ እየተገለገሉባት ስለሆነ በሥራ ሂደት አደጋ ቢደርስ ተጠያቂነቱን ማን መውሰድ አለበት የሚል ክርክር ሊያስነሳ የሚችልና በዚህ የተነሳም የማይገባ ዕዳ እንድንሸከም የሚያደርግ በመሆኑ መኪናዋ አገልግሎት መስጠቷ እንዲቀጥል መደረግ አልነበረበትም፡፡ ስለሆነም

በቀድሞው ትዕዛዝ መሠረት አገልግሎት መስጠቷ እንዲቆም ሊደረግልን ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን አቤቱታ ከተመለከተ በኋላ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙ ስምምነት ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ በማለት በመኪናዋ አጠቃቀም ላይ አመልካች የበኩላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ መጥሪያ ልኮላቸዋል፡፡ ይሁንና አጠቃቀሙን በተመለከተ ጊዜ ተሰጥቷቸው ሊስማሙ ባለመቻላቸው ፍርድ ቤቱ መኪናዋ በአገልግሎት መስጠት ሥራ ላይ ተሠማርታ መቆየቷ ሊመጣ ከሚችል አደጋ ጋር በተያያዘ በተጠሪዎች ላይ ከፍ ያለ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል በሚል ስጋት የቀረበለትን ምክንያት በመቀበል አገልግሎት መስጠቷ እንዲቆም እንዲደረግ በድጋሚ ትዕዛዝ አስተላለፏል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካች ለባህር-ዳር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነትን አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ለክርክሩ መነሻ በሆነችው ከፍ ሲል ቁጥሯ በተጠቀሰው መኪና መገልገል እንዲቀጥሉ እንዲፈቀድላቸው የሚጠይቅ ነው፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ለቀረበው አቤቱታ በሰጡት መልስ የወረዳው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ስለሆነ ይግባኝ ሊቀርብበት አይችልም፤ መኪናዋ ዕዳ አለባት የሚለው መከራከሪያ በማስረጃ ያልተደገፈ፤ የቀን ገቢዋን ለማወቅና ለመቆጣጠርም የሚያስቸግር፤ ዕዳ ለመክፈል የሚስችል የተሻለ ገቢ ያለው ሌላ ሃብት (ሱቅ) ያለ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ አቤቱታው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

እኛም የቀረበውን ክርክር ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም መልስ የሚሹት ጥያቄዎች የሥር ፍርድ ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነችው ሚኒባስ መኪና አገልግሎት መስጠት እንድታቆም በማድረግ ረገድ የሰጠው ትዕዛዝ የይግባኝ አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሰበር ወይም ይግባኝ አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል ከሆነ መኪናዋ ሥራ እንድታቆም በማድረግ ረገድ የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ግድፈት አለበት የለበትም? የሚለው ነው፡፡ እንደቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው እናያቸዋለን፡፡

የመጀመሪውን ጭብጥ በተመለከተ በፍትሐ-ብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 320 (3) ላይ እንደተመለከተው ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ትዕዛዛት የሥረ-ነገሩ ፍርድ ከመሠጠቱ በፊት ይግባኝ ሊቀርብባቸው እንደማይችል ተገልጿል፡፡ በምሳሌነትም ቀጠሮ የመለወጥ፣ ዳኘነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች ተጠቅሰዋል፡፡ የድንጋጌው ዓላማ በይዘታቸው ተከራካሪዎች ያሉበትን ሁኔታ (status quo) የማይቀይሩ ነገር ግን ዋናው ጉዳይ ዕልባት አግኝቶ በበላዩ ፍርድ ቤት በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ አብረው ሊታዩ የሚችሉት በይዘታቸው ፍጻሜን (finality) ያላገኙ ጉዳዮች ሁሉ በተናጥል እየቀረቡ እንዳይታዩ ለማድረግ ነው፡፡ ይህም በፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ ጉዳዮችን ፍሰት በመቆጣጠር አጠቃላይ የሆነው የዳኝነት አሠራር ሥልጠት ያለው እና ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ጉዳይ ይግባኝ

የሚቀርብበት ነው አይደለም? የሚለው ጥያቄ መታየት ያለበት በዚሁ መለኪያ መሠረት መሆን ይገባዋል፡፡

የአሁኑ ጉዳይም ከዚህ በተለየ መንገድ የሚስተገናድ አይደለም፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነችው መኪና አገልግሎት እንዳትሰጥ ሲደረግ የተሰጠው ትዕዛዝ አመልካች ከዋናው ፍርድ በፊት ያሉበትን የኢኮኖሚ ሁኔታ (economic position) የሚቀይር ነው፡፡ ገቢ ከማግኘት ወደማጣት፣ ከትጉ ዕዳ ከፋይነት ተስፋ በሚያስቆርጥ ደረጃ ከፍ ወዳለ ዕዳ ተሸካሚነት የሚያሸጋግር ይሆናል፡፡ በማህበራዊ ደረጃም ቢሆን ዝቅ ብለን በምንገልጸው ምክንያት በኢኮኖሚክ እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍ ያለ ተፅእኖን የሚያስከትል ነው፡፡ ያሉበትን ሁኔታ (status quo) በተመለከተም ውጤቱ ፍርድ እስኪገኝም ድረስ ቢሆን የማይተካ ጉዳትን በማስከተል ረገድ ፍፃሜ ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑ እንዲህ ያለ የተከራካሪዎችንም ሆነ አጠቃላይ የሆነውን ማህበራዊ ሁኔታ የሚያዛባ ሲሆን ጉዳዩ ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ፍሬ ነገር ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ነው፡፡ በአመልካችነት ከተቀመጠው ከአንቀጽ 320 (4) የምንገነዘበውም ይህንኑ ነው፡፡ ድንጋጌው በየቦታው ተሰባጥረው ከምናገኛቸው የሥነ-ሥርዓት ህጉ ዓላማዎች ከተገለጹበት አናቅጾች አንዱ ሲሆን በተከራካሪዎች መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ሚዛን በመጠበቅ ፍትህን ማስፈን እና በዚህ ውስጥም ማህበራዊውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በማሳለጥ ዓላማም ላይ የቆመ ነው፡፡ በዚህ የተነሳም የወረዳው ፍርድ ቤት ዕግድ እንዲነሳ የቀረበለትን ጥያቄ ሳይቀበለው የቀረበት ሁኔታ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተከራካሪዎች ያሉበትን የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚያዛባ እና የማይተካ ጉዳትን የሚያስከትል በመሆኑ ትዕዛዙ የይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ የሚችል ነው ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪው በዚህ ረገድ ያቀረቡትን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ወደሁለተኛው ጭብጥ ስንሸጋገር የዕግድ ትዕዛዝ ዓላማ ከፍርድ በፊት ተከራካሪዎች ያላቸውን የኢኮኖሚ ሚዛን (status quo) በመጠበቅ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከማሳካት አንፃር ለክርክር ምክንያት የሆነ አንድ ሃብት/ንብረት እንዲከበር ጥያቄ ሲቀርብ እንደነገሩ ሁኔታ የዕግድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ወይም ላይሰጥ ይችላል፡፡ የዕግድ ትዕዛዝ የሚሰጥ በሚሆንበት ጊዜ ግን የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳካት በሚያስችል ደረጃ ተገቢ በሆነው መጠን ብቻ መሠጠት ይገባዋል፡፡ ከዚህ አኳያ አሁን የቀረበውን ጉዳይ ስንመለከት የወረዳው ፍርድ ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነችው መኪና አገልግሎት መስጠት እንድታቆም የሰጠው ትዕዛዝ ተገቢነቱ ጥያቄን የሚያስነሳ ሆኖ ይታያል፡፡ ምክንያቱም የተጠቀሰችው ሚኒባስ መኪና እንዳትሸጥ፣ እንዳትለወጥ፣ ወይም በማናቸውም መንገድ ለሦሥተኛ ወገን እንዳትተላለፍ ታዟል፡፡ በጊዜው ሌላ ጥያቄ ያልቀረበ ከመሆኑ አንፃር ይህ በቂ ነበር፡፡ ገቢ በማጣት ረገድ ተጠሪ የሚደርስበት ጉዳት አለ የሚባል ከሆነም ጥያቄው ሲቀርብ ገንዘብ በማስያዝ ወይም በቂ የሆነ ዋስ በማቅረብ ወይም ሌላ አማራጭ በመከተል የተከራካሪዎችን የኢኮኖሚ ሚዛን መጠበቅ ይቻላል፡፡ ይህ ሳይሆን ወይም ከፍ ያለ ሚዛን የሚደፋ ጥቅም (compelling interest) አለ ሳይባል መኪናዋ አገልግሎት መስጠት እንድታቆም መደረጉ ተገቢ አልነበረም፡፡ ምናልባት አደጋ ሊከሰት ቢችል ባለዕዳ ልንሆን እንችላለን የሚለው ስጋት መኪናዋ እንድትቆም ለማድረግ በቀረበው ተመሳሳይ ምክንያት በቆመችበትም ቢሆን የተፈራውን የባለዕዳነት አደጋ ትዕዛዙ ለማስቀረት ያለው ሃይል

ዕምብዛም አይደለም (ግላዊ የሆነውን የተከራካሪዎችንና ማኅበራዊ የሆነው ዋጋ ግምት ውስጥ ሲገባ ማለት ነው)፡፡ ትዕዛዙ ህጉ የፈለገውን ውጤት ትርጉም ባለው መንገድ ለማስፈጸም ያለው ሃይል ሲመዘን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ሆኖ ይታያል፡፡ በተለይም ከፍ ሲል ከተጠቀሰው አማራጭ በተጨማሪ የሌላው ተከራካሪ ወገን ጥቅም ያለበት ሃብት በጁ ባለበት ጊዜ ለሚደርስ አደጋ የሚኖረውን ኃላፊነት ማን መውሰድ ይገባዋል የሚለውን በተመለከተ ህጉ በራሱ መፍትሄ የሚሰጥ መሆኑ ሲታሰብ መኪናዋ አገልግሎት መስጠት እንድታቆም የተሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ እንዳልነበረ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህን የምንለው ያለምክንያት አይደለም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሚዛን የሚደፉ ምክንያት ሳይኖር (without a rational ground) አመልካች ንብረቴ ነው በሚለው ሃብት የመገልገል መብቱን በመገደብ አመልካች ከፍርድ በፊት ያለውን የኢኮኖሚ ደረጃ (status quo) የሚያሳጣ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም መሠረታዊ የሆነ የፍትህ መዛባትን (fundamental miscarriage of justice) የሚያስከትል ይሆናል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፡፡ የመኪናዋ አገልግሎት መስጠት እንዲቋረጥ ለማድረግ የተሰጠው ትዕዛዝ ለህጉ ከተሰጠው ትርጉም አንፃር ሲታይ በአፈፃፀም ደረጃ አጠቃላይ በሆነው የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ውስጥ አንድን ንብረት ከአገልግሎት ሂደት ውስጥ በማውጣት በፍላጎትና በአቅርቦት ላይ ያለውን ሚዛን ሰው ሰራሽ በሆነ የማይገባ ጣልቃ ገብነት የተነሳ በተጠቃሚው ላይ የሚያስከትለው የኢኮኖሚ ጫና ከፍ ያለ ጉዳትን የሚያስከትል በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ ከግብር አሰባሰብ አንፃር ቢታይም ተመሳሳይ ጉዳትን የሚያመጣ ነው፡፡ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጧቸው ትዕዛዛት በተጠቀሱት ምክንያቶች መሠረታዊ የህግ ግድፈት ያለባቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም የባህር-ዳር ወረዳ ፍርድ ቤት ታህሣሥ 30 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ ሽረናል፡፡ በመሆኑም ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነችው ኮድ 3 የታርጋ ቁጥር 04539 አማ. የሆነችው ባለ አሥራ ሁለት መቀመጫ ሚኒባስ መኪና አገልግሎት እንዳትሰጥ የተሰጠው ትዕዛዝ በዚህ ውሳኔ ተነስቷል፡፡ ይህም ቀደም ሲል በወረዳ ፍርድ ቤት ትዕዛዙ ለተላለፈለት ለባህር-ዳር ትራፊክ ፖሊስ ጽ/ቤት ይገለጽለት፡፡ ይፃፍ፡፡ ይህ ትዕዛዝ ንብረቱ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ፤ ለሦሥተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የተሰጠውን ትዕዛዝ የሚመለከት ባለመሆኑ በዚህ ረገድ በወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ የተጠበቀ ነው፡፡

ተጠሪ ሊደርስብኝ ይችላል የሚሉት የኢኮኖሚ ጉዳት ካለ ይህንኑ በመግለጽ በሌሎች አማራጮች መብታቸው እንዲከበር ለማድረግ ያላቸውን መብት ይህ ውሳኔ አይገድበውም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔው የተሻረ መሆኑን እንዲያውቀውና በውሳኔው መሠረት እንዲያስፈጽም ግልባጩ ይተላለፍለት፡፡ ይፃፍ፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ለከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ይተላለፍለት፡፡ ይፃፍ፡፡

ኪሣራና ወጪ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡